# ሰውነትሽ በተፈጥሮው የተሟላ ነው



## እና ውበትሽ በእጅሽ ነው።

ማንም ሰው የሌላውን ሰው የሰውነት አካል የማስወገድ መብት የለውም

www.nkvts.no
Informasjonsbrosjyre om
kjønnslemlestelse på amharisk

ይህ በራሪ ወረቀት የተዘጋጀው በኖርዌይ በጥቃት እና ስር የሰደደ ጭንቀት ጥናት ማዕከል ነው (NKVTS)
በራሪ ወረቀቱ በዚህ በድህረ ገጽ www.nkvts.no የሚገኝ ሲሆን ሊያወረዱትም ይችላሉ

የታተሙ ቅጆዎችንም ከፈለጉ በዚህ (postmottak@nkvts.unirand.no) በኢ.-ሜይል አዘው እና በስልክ ቁጥር +47 22 59 55 00 ደውለው ማግኘት ይችላሉ።
የሴት ልጅ አባላተ ወሊድ መቆረጥን ለማስወገድ ከመንግስት የተግባር እቅድ ጋር በተያያዘ NKVTS የአባላተ ወሊድን ለማስወገድ ባለሞያዎችን በማሰባሰብ ብሔራዊ ማዕከል እንዲያቋቁም ተጠይቋል።

NKVTS ከሴት ልጅ አባላተ ወሊድ መቆረጥ ጋር በተያያዘ ጥናት የማካሄድ ግዴታ አለበት፣ በዚህ ዘርፍ ላይ ተዛማጅ ምክሮችን እና መረጃዎቸን ለኤክስፐርቶች እና ለባለሞያዎች መስጠት አለበት።
በዚህ ስልክ ቁጥር በመደወል ያገኙናል
+47 22 59 55 00
ተጨማሪ መረጃ ማንበብ ካስፈለግዎ ይህንን ድህረ ገፅ ይጎብኙ፣www.nkvts.no

ዲዛይን/ ግንኙነት፡ ክርስቲን ኢስታድ እና ካሪ ጃቬር ፒደርሰን

ማብራሪያዎች ገፅ 8-9: ካሪ ሲ.. ቶቬሩድ ሲኤ ምአይ (የተረጋገጠ የህክምና ማብራሪያ ሰጭ)
ፎቶዎች:ሉት እና ሲኦ ኤኤስ እና ላርስ ሶርሊ

# ሰውነትሽ የአንቺ ነው

ማንም ሰው ሰውነትሽን የመጉዳት መብት የለውም። የአንቺ ሰውነት ነው በሰውነትሽ ላይም ሃላፊነት ያለሽ አንቺ ነሽ። በህፃንነትሽ፣ በጨቅላነትሽ፣ ወይም በታዳጊነትሽ ጊዜ በዙሪያሽ ባሉ አዋቂዎች ላይ ነበር የምትደገፊው እናም አሁን በዚህ ጊዜም የምትረጂው ይህንኑ ነው።

አንዳንድ ልጃገረዶች የቤተሰብ ምኞቶች እና ፍላጎቶች ግፊት ይሰማቸዋል። ቤተሰብ የልጃገረዶች የወሲብ አካል ካልተገረዘ ማእረጋቸው እና ክብራቸው አደጋ ላይ እንደወደቀ ሊያስቡ ይችላሉ።
ይህ ሁኔታ አንቺን የሚመለከት ከሆነ፣ ኖርዌይ አንቺን ሊከላከል የሚችል አዲስ ህግ እንዳፀደቀች ማወቅ ይኖርሻል።

ከሚጎዳ ነገር የመጠበቅ መብት አለሽ። የሰውነትሽ አካል ንድ ጊዜ ከተወገደ በፍጹም በድጋሚ መልሰሽ ልታገኚው አትችይም።

አንቺ እራስሽ አናት በምትሆኚበት ጊዜ የልጅሽ የሰውነት አካል በተፈጥሮ እንደተሰራው የተሟላ እንደሆነ ማገናዘብ አለብሽ። የወሲብ አካልዋ የሰውነትዋ ኡደት አካል ሲሆን ሁሉም የሰውነት አካላት መልካም ህይወትን ለመምራት አስፈላጊ ናቸው።

ከአንድ ሰው ጋር ለመነጋገር ካፈለግሽ፣ ወይም እርዳታ ካስፈለገሽ፣ የመገናኛ መረጃ በበራሪ ወረቀቱ መጨረሻ ላይ ይገኛል።

ሰውነትሽ ተፈጥሮ እንደሰራው የተሟላ ነው



# የአባላተ ወሊድ መቆረጥ ጤንነትዎን አደጋ ላይ ይጥላል

የአባላተ ወሊድ ግርዛት ባህላዊ ሲሆን የሴቶችን የውጫዊ የወሲብ አካልን ማለትን ቂንጥርን ከቆረጡ በኋላ የማስወገድ ሂደት ነው። የሂደቱ አሰረጫጨት በሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ነው እንዲሁም በሰፊው የተለያየ ነው። ድርጊቱ የሚከናወነው እድሜቸው ከ5 እስከ 14 ዓመት እድሜ ባላቸው ልጃገረዶች ላይ ሲሆን ነገር ግን አልፎ አልፎ አዲስ በተወለዱ ህፃናት ላይም ይካሄዳል።

የአባላተ ወሊድ መቆረጥ "ግርዛት" "ሱና"ተብሎ ይጠራል እንዲሁም ሌሎች የሚጠራበት ስሞች አሉ። የልጃገረዶች የአባላተ ወሊድ መቆረጥ በከፍተኛ ደረጃ አደጋ ያለው ሲሆን ወንድ ልጆችን ከመግረዝ በበለጠ የተሰራጨ ነው። በሌላ አባባል፤ ሁለቱ ሂደቶች እኩል አይደሉም።

ኖርዌይ ማንኛውንም አይነት የአባላተ ወሊድ መቆረጥን ታወግዛለች። ትልቅም ሆነ ትንሽ የሰውነት አካል ቢወገድ ምንም ለውጥ የለውም፣ ህገወጥ ነው። የጤነኛ ልጃገረድን የወሲብ አካል ለመቁረጥ ምንመ መልካም ምክንያት የለም።

የአባላተ ወሊድ መቆረጥ የልጃገረድንም ወይም የሴትን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል ነው እስከ ህይወት መጨረሻ ድረስ የሚቆይ ጉዳትን ያስከትላል። በብዙ ሃገራት ክልክል ነው። ኖርዌይ አለም አቀፍ ኮንቬንሽኖችን ፈርማለች፣ እንዲሁም በቁርጠኝነትም የህዝቦችን ጤንነት እና ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥሉ ባህሎችን ለማጥፋት ተነስታለች። በተጨማሪም የአባላተ ወሊድ መቆረጥን የሚያግድ ህግ አለን። ይህም በስራ ላይ የዋለው ኖርዌይ ውስጥ የሚኖሩ ልጃገረዶች እንዲህ ካለው ሂደት ይጠበቁ ዘንድ ነው።

ወጣቶች ስለ ሴት ልጅ የአባላተ ወሊድ መቆረጥ (ግርዛት) ማውራት ከባድ ሊሆንባቸው ይችላል ምክንያቱም በጣም አስነዋሪ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው።. የወሲብ አካላቸው ያልተቆረጠ ልጃገረዷች ስለዚህ ባህል የበለጠ ለማወቅ ይፈልጉ ይሆናል። እህቶች እና ጓደኞች አደጋ ላይ ስለሆኑ ይጨነቁ ይሆናል እናም የበለጠ ለማወቅ ይፈልጋሉ። ይህ በራሪ ወረቀት የሚነግርዎት፤

- የሴት ልጅ አባላተ ወሊድ መቆረጥ ምን እንደሆነ
- ስለ የሴት ልጅ አባላተ ወሊድ መቆረጥ ሃሳቦች
- በተፈጥሮ የሰውነት አካልን እንዴት መሆን እንዳለበት
- የሴት ልጅ አባላተ ወሊድ መቆረጥ የጤንነት አደጋዎች
- በኖርዌይ ውስጥ የሴት ልጅ አባላተ ወሊድ መቆረጥን የሚያግድ ህግ እርዳታን ለማግኘት የት መሄድ ይችላሉ



Foto: Lars Sørli

# ስለ የሴት ልጅ አባላተ ወሊድ መቆረጥ ሃሳቦች

**የሴት ልጅ አባላተ ወሊድ የመቆረጥ ተግባራትን የሚያከናውኑ ሰዎች ለምን አስፈላጊ እንደሆነ የሚያምኑባቸውን የተለያዩ ማብራሪያዎች አሏቸው። በሰፊው የሚታመንባቸውን ጥቂት አመለካከቶች እዚህ አስቀምጠናቸዋል።**

### የሴት ልጅ አባላተ ወሊድ መቆረጥ የልጃገረዷን ወሲባዊ ሞራል ይጠብቃል

የሴት ልጅ አባላተ ወሊድ መቆረጥ የወሲብ ግላጎትን አይቀንስም ምክንያቱም የወሲብ ፍላጎት ያለው በአዕምሮ ውስጥ እና በቅርጸተ ሃሳብ ውስጥ ነው። የሴት ልጅ የወሲብ አካል መቆረጥ ከጋብቻ በፊት ያለ የግብረ ስጋ ግንኙነትን አይከላከልም እንዲሁም አለመታመንን አይከላከልም። የወሲብ አካል ባለመቀየሩ ምክንያት የወሲብ ፈላጎትን መቆጣጠር እና ታማኝ መሆን ከባድ አይደለም። ከጋብቻ በፊት ወይም በጋብቻ ውጭ የአቋም እና የአመለካከት ጥያቄ ነው።

### የሴት ልጅ አባላተ ወሊድ መቆረጥ ያረጀ ባህል ነው፣ እና ሁሉም ሰው ያካሂደዋል። ከሌሎች መለየትን ለማስቀረጥ የልጃገረዶች የወሲብ አካል መቆረጥ አለበት

አብዛኛው የአለም ህዝብ ከሴት ልጅ የወሲብ አካል መቆረጥ ውጭ ይኖራል።. ጎጂ ችግር እንደሚያመጣ የሚያሳውቁ መረጃዎች ይህን ሂደት የመቃወም አን የማገድ ቁጥሩን ጨምሮታል። እንዲሁም በብዛት በሚከናወንባቸው ማህበረሰቦች ውስጥም ጨምሮ ።

### “ነገር ግን በጣም ትንሽ ቁራጭ ብቻ ነው የምንወስደው”

አብዛኞቹ ከውጫዊው ከሴት ልጅ የወሲብ አካል (ቂንጥር) “ትንሽ ቁራጭ” መውሰድ ነው የሚፈልጉት፣ በአብዛኛው ”ሱና” ተብሎ በሚጠራው ሂደት አማካኝነት። ነገር ግን “ትንሽ ቁራጭም” ቢሆን ከባድ እና ወሳኝ ጉዳትን ሊያስከትል ይችላል። ይህ ሌላው ምክንያት ነው እንዲህ ያለው ሂደት ነው በግዴለሽነት የሚታየው ስለዚህም መታገድ አለበት ። ስለዚህ ለምን አንድ ነገር ጎጂ እንደሆነ እና አላስፈላጊ እንደሆነ ከታወቀ በአጠቃላይ አይወገድም? አንዳንድ ባለሞያዎች ቂንጥርን እና የውስጠኛው የእምስ ከንፈርን ያስወግዳሉ (የውስጠኛ ‘ከንፈር’ የእምስን ዙሪያ የሚሸፍን) እና እንዲህም ሆኖ “ትንሽ ጨፍ” ብቻ ነው የምንወስደው እያሉ ይቃወማሉ። በዚህ ህኔታ ሁለቱም ቤተሰቦችም ሆነ ልጃገረዶቹ ተታለዋል ምክንያቱም ይህ ሂደት እነሱ ከሚያስቡት እና ከሚፈልጉት በላይ የተወሰደ ነው።

### ያልተቆረጡ ሴቶች ባል አያገኙም

የሴት ልጅ ግርዛት በሚካሄድባቸው ሃገራት ውስጥ ያሉ ብዙ ወንዶች ምን ያህል ጎጂ እንደሆነ ይረዱታል። የምስቶቻቸው አባላተ ወሊድ እንዲቆረጥ አይፈልጉም ። የአባላተ ወሊዳቸው ያልተቆረጠ ሴቶችን ችግር የማጋጠሙ ሁኔታ አነስተኛ ነው።

### ወላጆችዎን እና ባህሉን መታዘዝ ትክክል ነው

ጎጂ ልማዶች መወገድ አለባቸው።
የሴት ልጅ ግርዛት ጎጂ እና ህገ ወጥ ነው። ቤተሰቦችሽ እንድትቆረጪ ካደረጉሽ፣ ምንም አንኳ ስለሚያፈቅሩሽ ቢሆንም፣ አንቢ ለማለት ህጋዊ መብት አለሽ። ለመከላከል እርዳታ ማግኘት ትችያለሽ፡ በዚህ በራሪ ወረቀት ላይ ያለውን ዝርዝር ተመልከቺ።

### የሴት ልጅ ግርዛት በሃይማኖት ይፈለጋል

ምንም አይነት ሃይማኖት የሴት ልጅ ግርዛትን አይደግፍም/አይፈልግም። በአንጻሩ ግን፣ ብዙ ሃይማኖቶች ተፈጥሮን ላለማበላሸት ሲሉ እንዳይደረግ ይመክራሉ። አንዳንድ ሙስሊሞች እስልምና የሴት ልጅ ግርዛትን እንደሚደግፍ ያምናሉ።



# ሰውነት እንዴት ነው በአንድ ላይ የተቀመጠው

## ተፈጥሮአዊ የሴቶች የወሲብ አካላት

የሴትን አካለ ወሊድ መዝጋት አስፈላጊ አይደለም ምክንያቱም ተፈጥሮ በራሱ አስተካክሎ ዝግቶታል። የሴት የወሲብ አካላት የራሳቸው የሆነ እና የተወሰነ ስራዎች አላቸው እናም ሰውነት በተመቻቸ ሁኔታ የተሟላ ነው።




ቂንጥር፣ የእመስ መከፈቻ እና የማህጸን መከፈቻ ሁለም የእምስ መሸፈኛ ከንፈር ወደ ታች ሲሆን ብቻ በሚገባ ይታያሉ




**ቂንጥር**
በጣም ወደ ውስጥ የታጠፈ አካል እና ስሜታዊ ክፍል ነው። አብዛኛውን ጊዜ ቂንጥር በሰውነት ውስጥ ተደብቀው አይታዩም። የሚታየው የላይኛው ክፍል ወይም ጫፉ ነው። የአተር ግማሽ የሚሆን መጠን አለው።

**የማህጸን መከፈቻ**
**የማህጸን መከፈቻ**
የሚገኘው በቀጥጣ ከእመስ መከፈቻ ፊት ለፊት ነው።

**የእምስ የላይኛው እና የታችኛው ክፍል**
እምስን እና ማህጸንን ይሸፍናል እንዲሁም ይከላከላል

**የእምስ መከፈቻ**
እምስ እና የእምስ መከፈቻ ከልጅ መውለድ ጋር በተያያዘ የሚተማጠፍ እና ሊለጠጥ የሚችል ነው፣ ለምሳሌ

**የቂንጥር መከለያ**
የቂንጥርን እራስ ይሸፍናል እንዲሁም ይ ከላከላል

**የእምስ የላይኛው ክፍል**
ለእምስ የውስጠኛው ወይም የታችኛው ክፍል እና ለሌሎች በአካባቢው ላሉ አካሎች ሽፋን ይሰጣል። በአብዛኛው የእምስ መከፈቻ እና የማህጸን መከፈቻ የሚሸፈኑት በእምስ የላይኛው አካል ነው።

**ደንግልና**
በእምስ ዙሪየ ያለ ቀጭን የፈሳሽ አካል ከማህጸን መከፈቻ መገናኛ ቱቦ ቦታ ላይ ያለ። የእምስ መግቢያው ወንዶች አካለ ወሊዳቸውን ወደ ውስጥ ለማስገባት እና ለማስወጣት ይረዳቸዋል። በአጠቃላይ፣ የግብረስጋ ግንኙነት (የመጀመሪያ የግብረ ስጋ ግንኙነትን ጨምሮ) በደንግልና ላይ ምንም አንደ መቀደድ ያለ ጎጂ ነገር ሳያደርጉ የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ ይቻላል።



# የሴቶች የአካለ ወሊድ መቆረጥ (ግርዛት) አይነቶች

ይህ የሴቶች አካለ ወሊድ መቆረጥ አመዳደብ በዓለም የጤና ድርጅት የአመዳደብ አይነት ላይ የተመሰረተ ነው። በገሃዱ አለም የተለያዩ አይነቶች የሚፈጠሩ ሲሆነ በአብዛኛው አንዱ ከእንዱ ጋር ይመሳሰላል።

**አይነት I:** ክሊትሮዴክቶሚ፡ የቂንጥር በግማሽ ወይም ሙሉ በሙሉ መቆረጥ። አንዳንድ ጊዜ እርግጠና ለመሆን ያስቸግራል

**አይነት II:** ኤክሲሽን፡ ግማሽ ወይም የቂንጥር እና የእምስ የውስጠኛው ክፍል በአጠቃላይ መወገድ



አይነት II

**አይነት III:** መስፋት ፡ የእምስን መሸፈኛ በመስፋት ማጥበብ እና ሽፋን መስራት ። መሸፈኛው የሚሰራው የእምስን የውስጠኛውን ወይም የላይኛውን ክፍል ቆርጦ ቦታውን በማስተካከል ቂንጥርን አስወግዶም ሆነ ሳያስወግዱ መፈጸም ይቻላል።




አይነት III

**አይነት IV:** ሌሎች የሴት አባላተ ወሊድን ከህክምና ምክንያት ውጭ የመለወጥ ሂደቶች ለምሳሌ፡ የሴት ልጅን የአባላተ ወሊድ አካባቢ ማስቧጠጥ፣ ማስበሳት፣ ማስቦጨቅ እና ማስተኮስ

# በጤንነት ላይ ያለው ተፅእኖ

የችግሮቹ አይነት እና የመከሰታቸው ሁኔታ በሂደቱ አይነት ላይ የተመሰረተ ሲሆን፣ የልጃገረዷ እድሜ፣ እና ሌሎች ሁኔታዎች እንደ የሰውነት ሁኔታ፣ የንጽህና ደረጃ ወዘተ የተለያየ ነው። በቤተሰብ፣ በማህበረሰብ እና የመኖሪያ አካባቢ ያለ የሰዎች አቋምም ተልቅ አስተዋፅኦ አለው። የግርዛት ሂደቱ በሆስፒታል ወይም በባህላዊ ዘዴ ቢካሄድም ሁለቱም ዘዴዎች ችግር ሊያስከትሉ ይችላሉ። አንዳንድ ችግሮች ለአጭር ጊዜ ብቻ የሚቆዩ ወይም ጊዜያዊ ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ደግም ለረዥም ጊዜ የሚቆዩ እና ስር የሚሰዱ ሊሆኑ ይችላሉ።

## ጊዜያዊ ወይም ለአጭር ጊዜ የሚቆዩ ችግሮች

- ከባድ ህመም
- ክፍት የሆነ ቁስል እና የተመረዘ ቁስል
- ከባድ የሆነ እና እስከ ሞት የሚያደርስ መድማት (ብኡ ደም መፍሰስ)
- የሽንት መሽናት ችገር በእብጠት እና በሽንት ቱቦ ላይ በሚፈጠር ጉዳት ምክንያት
- እስከ ሞት የሚያደርሱ ኢንፌክሽኖች
- በግርዛቱ ሂደት ህመሙ ከባድ በመሆኑ ምክንያት ልጅአገረዷን በሃይል ለመያዝ እና ለመግረዝ በሚደረግ ጥረት ላይ የሚከሰቱ የመሰንጠቅ እና ሌሎች ጉዳቶች።



## ለረዥም ጊዜ የሚቆዩ ወይም ስር የሰደዱ ችግሮች

- የሆድ ህምም እና የማያቋርጥ የታችኛው የሆድ ክፍል ህመም
- የተጨማደደው የሰውነት አካል ጠባሳ እና ህመሙ ለመንቀሳቀስ የሚያግድ ሲሆን በተጨማሪም ለመጫወት እና ስፓርት ለመስራት ያዳግታል
- በማህጸን ውስጥ የወር አበባ የደም ቱቦዎች ህመም እና ተዛማጅ ህመም (ከመቆረጡ በኋላ)
- የመሽናት ችግር እና ህመም፣ የሽንት መፍሰስ እና የማያቋርጥ የደም መፍሰስ
- የመገናኛ አካል እጢ ወይም የሲስት ማደግ (በፈሳሽ የተሞላ ወይም እጢ) ጠባሳው ባለበት የሰውነት አካል ላይ
- ፊስቱላ (የሽንት ቱቦ እና የማህጸን መገናኛ አለአግባብ መገናኘት እና/ወይም የፊንጢጣ) ሰገራ መቆጣጠር ወደ አለመቻል ይዳርጋል (መደበኛ የፊንጢጣ መቆጣጠሪያን ማጣት) እና ሽንትን አለመቆጣጠር (የሽንት መፍሰስ)
- ሂደቱ የግብረ ስጋ ግንኙነትን ስሜት የሚቀንስ ሲሆን ወይም ደግሞ በግብረስጋ ግንኙነት ጊዜ በቀላሉ ህመም የመሰማት እና ምቾት አለመኖርን ይፈጥራል
- የመጸነስ ችግሮችን፣ ከማህጸን በላይ እርግዝና የመከሰት እድል የመጨመር ሁኔታ (የዳበረ እንቁላል ከማህጸን ውጭ ሲያድግ)
- በእርግዝና ጊዜ የእርግዝና ችግሮች እና የወሊድ ችግሮች የመከሰቱ ሁኔታ ከፍተኛ ነው። በጥቂት አጋጣሚዎች፣ የሁለቱም የእናትም ሆነ የልጅ ህይወት በአደጋ ላይ ሊሆን ይችላል
- የመጀመሪያ እንክብካቤ በሚሰጥ እና ከፍላጎት ውጭ ወይም ያለማስጠንቀቂያ አንዳች ነገር ለማድረግ በሚያስገድድ ሰው ላይ እምነት ማጣት
- በህይወት ውስጥ ያለ ቀጣይ ክስተት ከሂደቱ ጋር በተያያዘ ከባድ ፍርሃትን ይጭራል። ክስተቶቹ ከግብረ ስጋ ግንኙነት ጋር የተያያዙ እንቅስቃዎች፣ መውለድ እና የማህጸን ምርመራ።

# ታሪክ እና መዘውተር

ማንም ሰው በእርግጠኝነት የሴቶች የአባላተ ወሊድ የመቆረጥ ልማድ እንዴት እና ለምን እንደተጀመረ አያውቅም። የምናውቀው ነገር ቢሆር ለብዙ ሺህ አመታት እንደነበረ እና ከክርትና እና ከእስልምና መምጣት በፊትም እንደነበረ ነው።

የአባላተ ወሊድ መቆረጥ በእስልምና፣ በክርስትና ሃማኖት ተከታዮች እንዲሁም በሌሎች የእምነት ማህበረሰብ የሚካሄድ ነው። በተመሳሳይ፣ በአለም ላይ ያሉ አብዛኞቹ ሙስሊሞች እና አብዛኞቹ ክርስቲያኖች ያልተገረዘች ልጅ የላቸውም።

ምንም አይነት ሃይማኖት ወይም እምነት ልጃገረዶች እንዲቆረጡ አይፈልግም

የአባላተ ወሊድ መቆረጥ የሚካሄድባቸው ማህበረሰቦች የሚከተሉት ለብዙ አመታት የቆዩ ልማዶች አሏቸው፡ የአባላተ ወሊድ መቆረጥ እውነተኛ ወይመ የባህል የተፈጥሮ ክፍል ነው። በአንዳንድ የህብረተሰብ አካለት ውስጥ፣ የአባላተ ወሊድ መቆረጥ የሴት ልጅን የግብረ ስጋ ግንኙት የመቆጣጠርያ ዘዴ ነው። ቸልተኝነት፣ በተለይም ስለ ህክምና ችግሮች፣ ባህል እንዴት መቆየት እንደቻለ ያብራራል። ያረጀ ባህል ነው፣ እናም አካባቢያዊ ማህበረሰቦች ሂደቱን ለማበረታታት ከፍተኛ ግፊት ያደርጋሉ።

ልማዱ በአፍሪካ አህጉር ውስጥ በስፋት ተዛምቷል፣ ነገር ግን በመካከለኛው ምስራቅ፣ በኢንዶኔዥያ በማሌዥያ እና በህንድ ህዝቦችም በተግባር ላይ ይውላል።

አንደ የዓለም የጤና ድርጅት በዓለም በየዓመቱ ከ130-140 ሚሊዮን የሚሆኑ ሴቶች እና ልጅአገረዶች የአባላተ ወሲብ መቆረጥ ይፈጸምባቸዋል። በዚህ አለም አቀፍ ጉዳይ አይነት I, II እና IV ከጠቅላላው 90 በመቶ የሚሆነውን ይሸፍናሉ።. አይነት III 10 በመቶ የሚሆነውን በቻ ነው የሚሸፍነው። አይነት III በኖርዌይ ከፍተኛ ቁጥር አለው ነገር ግን ይህ ሊሆን የቻለው ይህ ድርጊት እንደባህል የሚቆጠረበት አገሮች የሚመጡ ሰደተኞች በብዛት ስለሚኖሩ ሊሆን ይችላል።



ይህ የአለም ካርታ የሴት ልጅ አባላተ ወሲብ መቆረጥ የሚፈጸምባቸውን ቦታዎች ያሳያል። የተግባሩ ቁጥር ከጠቅላላ የሴቶች ቁጥር 20 በሞቶ በታች የሆኑ አገሮች አልተካተቱም።.

- ከጠቅላላ የሴቶች ብዛት ከ 20–49 በመቶ
- ከጠቅላላ የሴቶች ብዛት ከ 50–79 በመቶ
- ከጠቅላላ የሴቶች ብዛት ከ 80+ በመቶ



# ህጉ ምን ይላል

የሴት ልጅ አባላተ ወሊድ የመቁረጥ ሂደት ጋር የተያያዙ ተግባሮችን የሚከለክለው ህግ በስራ ላይ የዋለው በ1996 ነው እናም ማንኛውንም አይነት የአካለ ወሊድ መቆረጥ ይከለክላል። ህጉ ሁለት ክፍሎች አሉት። የመጀመሪያው የሴት ልጅ አባላተ ወሊድን መቁረጥ የሚከለክል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተግባሩን መቀየር ወይም መካላከል ነው።

## እገዳው

በኖርዌይ ውስጥ እየነሮሽ የአባለተ ወሊድ መቆረጥ ከተፈጸምብሽ እናም ዎላጆሽ ይህንን መከላከል ይችሉ ከነበረ ወላጆችሽ ወንጀል ፈጽመዋል ማለት ነው። ማንኛውም የአባለተ ወሊድን የመቁረጥ ተግባር የሚፈጽም እንዲሁም በአፋጻጸሙ ላይ የተሳተፈ ለቅጣት ይዳረጋል። ይህ ማለት ኖርዌይ ውስጥም ይሁን ሌላ ቦታ ወላጆችሽም ሆኑ ሌላ ማንኛውም ሰው ይህንን ተግባር ወደሚፈጽም ሰው ሊወሰዱሽ አይችሉም።

§1

ማንኛውም ሰው የሴት አካለተ ወሊድን የሚጎዳ ወይም ቋሚ የሆነ ለውጥ የሚያመጣ ቀዶ ጥገና በፈቃደኝነት የሚፈጽም ይቀጣል። ቀዶ ጥገናው ህመምን ወይም ከሁለት ሳምንት በላይ ከመሰራት የሚያግድ ከሆነ ወይም ለመጠገን የማይቻል ጉዳት፣ መዛባት፣ ወይም ቁስል ወይም በስምንት አመታተወ ውስጥ ሞትን ካሰከተለ ከስድሰት አመታት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ከሶስት አመት ለማይበልጥ ጊዜ በእስራት ያስቀጣል። ተባባሪዎችም ለተመሳሳይ ቅጣት ይዳረጋሉ። የሴት አካለተ ወሊድን የመቁረጥን ስራ የመጠገን ስር ማከናወንም ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ መሰረት ያስቀጣል።

ከቤተሰቦችሽ ጋር የማትኖሪ ከሆነ እና እነዚህ አሳዳጊዎችሽ ይንን ሂደት መፈጸም ግዴታቸው እንደሆነ ሊያስቡ ይችላሉ። የሚያደርጉት ነገር እምነታቸው የሚጠብቅባቸው እንደሆነ ለማሳመን ሊሞክሩ ይችላሉ። ስለዚህ በባእላት ጊዜ ከአያቶችሽ፣ ከእንጀራ እናትሽ/አባትሽ ወይም ከሌሎች ጋር በምትኖሪበት አገር ወይም በወላጆሽ አገር ሰትቆይ ሊያጋጥሙሽ ስለሚችሉ አደጋዎች ማወቅ ያስፈልጋል።

ብልትን በወሊድ ምክንያት ከተከፈተ በኃላ መልሶ መዝጋት ማለትም ከንፈሮቹን አንድ ላይ አያይዞ ደግሞ መሰፋት ወንጀል ነው።



## የመከላከል ወይም የማስቆም ሃላፊነት

ሂደቱን የመከላከል ወይም የማስቀረት የሴት ልጅ አካለ ወሊድ መቆረጥን የማስቀረት ወይም የመከላከል ሃላፊነት በተለያዩ በህዝብ እና በግሉ ዘርፍ ላይ ባሉ ተቀጣሪዎች ላይ ወድቋዋል።

አንድ ሰራተኛ አንድ ሰው የአባለተ ወሊድ የመቆረጥ አደጋ ከተጋረጠባት የማስቆም ወይም የመከላከል ሃላፊነት በህግ ተጥሎበታል። ለምሳሌ የህጻናት የበጎ አድራጎት ባለስልጣናትን ወይም ፖሊስ በማሳወቅ ይህ ማንኛውንም ሚስጥር የመጠበቅ ሃላፊነት ይሰርዛል።

§2 በልጆች እንክብካቤ ማህከል ውስጥ፣ በልጆች በጎ አድራጎት አገለግሎት ውስጥ፣ የጤና እና ማህበራዊ በጎ አድራጎት አገለግሎት ውስጥ ትምህርተ ቤቶች ወስጥ, ለተማሪዎች የቀን እንክብካቤ በሚያቀርቡ ተቋሞች ውስጥ እና በሃይማኖታዊ ድርጅቶች ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች በፈቃደኝነት ወይም እያወቁ የሴት ልጅን አባላተ ወሊድ መቆረጥን በመደኛ ማመልከቻ ወይም በሌላ መልክ ለማስቆም ወይም ለመከላከል ያልቻሉ ባለሞያዎች እና ሰራተኞች በሲ..ኤፍ ክፍል 1 መሰረት ቅጣት ወይም ከአንደ አመት ያላልበለጠ እስር ሊጣልባቸው ይችላል። ይህ ህግ በአረጋዊያን ወይም በሃይማኖት መሪዎች በተመሳሳይ ተፈጻሚ ይሆናል። ይህንን ተግባር የመቀልበስ ተግባር ማንኛውንም ሚስጥርን የመጠበቅ ሃላፊነትን አያጠቃልልም። የሴት ልጅን አካለ ወሊድ ካልተቆረጠ ወይም ለቅጣት የሚጋርድ ጥፋት ካልተፈጸመ ቅጣት አይኖረውም።

ስለ የሴት ልጅ አካለ ወሊድ መቆረጥ መመካከር ወይም የአካለ ወሊድ መቆረጥ እንዳይፈጸም ድርጊቶቸን ማስቀረትን ወይም ማስቀየርን ችላ ማለት የሚያስቀጣ ጥፋት ነው ። ነገር ግን የአካለ ወሊድ ተቆርጠ መገኘት ህገ ወጥነት አይደለም።

## መረጃን የማሳታወቅ ሃላፊነት

የአባለተ ወሊድ እንክብካቤን በከፍተኛ ሁኔታ ማጓደል/መተላለፍ ነው። አባለተ ወሊድ መቆረጥን ከመከላከል በተጨማሪ የመንግስት እና የግል ሰራተኞች እንክብካቤ ማጓደልን/መተላለፍን ለህጻናት በጎ አድራጎት አገልግሎት የማሳወቅ ህጋዊ ግዴታ አለባቸው። እርሶዎ ራስዎ የአባለተ ወሊድ መቆረት ሰለባ ሊሆኑ ይችላሉ ወይም እህትዎ አደጋ ላይ ልትሆን ትችላች፣ እርሰዎ ወይም የእርሶዎ ልጆች ክክንወኑ በሁዋላ ተገቢውን የህክምና እርዳታ ባለማግኘት ምክንያት በሚከተል የጤንነት መወሳሰብ

## የምክር አገልግሎት እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የጤና ምርመራ

ከ መህር 2009 አንስቶ የተመረጡ መዘጋጃ ቤቶች የልጃገረዶች ወይም የሴቶች አባላተ ወሊድ መቆረጥ ከ30 በመቶ ወይም ከዚያ በላይ ከሆነባቸወ አገራት ለሚመጡ የጤና ምርመራ ያቀርባሉ። በኖረዌይ የመጀመሪያ አመት ቆይታቸው አገልግሎቱ ለሁሉም ይቀርባል።.
ከነዚህ አገራት የመቱ ወላጆች ለጃቸው (ልጆቻቸው) ትመህርት ሰትጀምር(ሩ) እና አምሰተኛ ክፍል ሰትደርስ (ሲደርሱ) ሰለ የሴት ልጅ አባላተ ወሊድ መቆረጥ ምክር ይሰጣቸዋል። በተጨማሪም ልጃቸው የጤና ምርምራ እንዲደረግላት ማድረግ ይችላሉ።

በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ውስጥ የሚማሩ ልጃገረዶች ከአማካሪ ጋር የመነጋገር እና በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የጤና ምርመራ የማግኘት እድል ይኖራቸዋል።

ከምርመራው በፊት ልጅቷ ወይም ወላጆቿችዋ በጽሁፍ ስምምነተቻውን መግለጽ አለባቸው። በ2010 ምክር እና የጤና ምርምራ በአገሪቱ በሙሉ ይቀርባሉ።



ለበዙዎች፣ የሴት ልጅ የአካለ ወሊድ መቆረጥ በደንብ የተጠበቀ ሚስጥር ነው። በአሰራዎቹ ውስጥ ያሉ ልጃገረዶች ስለ የሴት ልጅ ግርዛት የተለያዩ ነገሮችን መዋቅ ትፈልግ የሆናል ነገር ግን ጓደኞችዋን ወይም የምታውቃቸውን ለመጠየቅ ትፈራለች። የትምህርት ቤት ነርሶች (helsesøster) ወይም ዶክተሮች ስለ ጉዳዩ በሚገባ ማወቃቸው አሰፈላጊ ነው እንዲሁም ሚስጥር ለመጠበቅ ቃለ ማህላ መፈጸማቸው ጠቃሚ ነው፣ የግርዛት ሰለባ ነኝ ብላው ካሰቡ ፈቃደኛ ድርጅቶች እና የመንግስት ወኪሎች ሊረዱ ይችላሉ። ስምዎን ወይም ማንነትዎን ማወቅ ሳያስፈልጋቸው ለጥያቄዎችዎ መልስ ይሰጣሉ።

## ከሚከተሉት እርዳታ ማግኘት ይችላሉ፣

- በትምረት ቤትዎ ወይም ከሚኖሩበት አካባቢ መዘጋጃ ቤት ያለ የመንግስት ነርስ ወይም የበጎ አደራጎት መምህር (sosiallærer)
- የጠቅላላ ሃኪምዎ ወይም ማንኛውም ይህክና ዶክተር
- የቀይ መስመር እርዳታ ስልክ 815 55 201 ስምዎን/ማንነትዎን ሰይገልጹ መደወል ይችላሉ
- በአካባቢዎ የሚገኘው መዘጋጃ ቤት የልጆች በጎ አደራጎት አገልግሎቶች
- የፖሊስ የእርዳታ ስልክ 02800

## በድህረ ገጽ ላይ መረጃ:

www.ung.no www.seif.no www.nkvts.no

## የጤና ክልሎች (helseregioner)

በማንኛውም ጤና ክልል ውስጥ የሴቶች ክሊኒክ (kvinneklinikk) አለ። እነዚህ ክሊኒኮች የአከለ ወሊድ መቆረጥ የተፈጸመባቸውን ልጃገረዶች እና ሴቶች መረዳት ይጠበቅባቸዋል። ማማከር፣ አካላዊ ምርመራ፣ ህክምና እና ቀላል የማስተካከል ቀዶ ጥገና ይሰጣሉ። በቀጥታ እነዚህን ክሊኒኮች ሊጎበኙ ይችላሉ ወይም ከዶክተር፣ ከትምህርት ቤት ነርስ ወይም ከአዋላጅ ወደነዚህ ክ ሊኒኮች ሊላኩ ይችላሉ። ክሊኒኮቹ ሚስጥርዎትን ሊጠብቁ እና ለጥያቄዎ መልስ ሊስጡ ቃል ገብተዋል። በሰሜን ኖርዌይ የሚገኘው ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል(UNN), Tromsø የማህጸን ሃኪም ፣ የተመላላሽ ታካሚዎች ክፍል፣ የድህረ ወሊድ ተመላላሽ ታካሚዎች ክፍል፣ ወይም የእና ቶች ዋርድ ለማግኘት 77 62 60 00 ይደውሉ።

ሀውክላን የኒቨርሲቲ ሆስፒታል፣ በርግን በሆስፒታሉ ስልክ ቁጥር 05300 ደውለው የሴቶች ክሊኒኩን (kvinneklinikken) ይጠይቁ

የቅዱስ ኦላፍ ሆስፒታል፣ ትሮንዲም የሴቶች ክሊኒክ ለማግኘት 72 57 12 12 ይደውሉ።

ሰታቫነገር ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል የሴቶች ክሊኒክ ለማግኘት 05151 ይደውሉ።

ኦስሎ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል፡ የሴቶች ክሊኒክ ቀጥታ መስመር 22 11 98 44 እንዲሁም ሳራ ካህሳይ የም ክር አገልግሎት 93 89 89 03

ኦስሎ ዩኒቨርሲቲ ሆስፒታል ሪከሰሆሰታሌት ዋናውን የሆስፒታል ስልክ ይደውሉ 23 07 00 00 ከዚያም የ ሴቶች ክሊኒክን ይጠየቁ



ልጆች ራሳቸውን እንዲያውቁ ይርዱ

Nasjonalt kunnskapssenter om vold og traumatisk stress



# ሰዎነትዎ የርስዎ ነው

Nasjonalt kunnskapssenter
om vold og traumatisk stress